# “ልማታዊ መንግስት” — ዴሞክራሲን በልማት የመቆመር ፖለቲካ

(በአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)
ahayder2000@gmail.com

## መግቢያ

ባለፈው የኅብረ-ብዕር እትም ላይ በኒዮሊበራሊዝም ጽንሰ ሃሳባዊ ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥና በዓለም ላይ በታየው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሁኔታዎች ዙሪያ የሚያተኩር ጽሑፍ ማቅረቤ ይታወቃል፡፡ በዚህ በሁለተኛው ክፍል ጽሑፌ ደግሞ በልማታዊ መንግስት ንድፈ ሃሳብ ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥና በዓለም ላይ በታየው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ክርክሮች ዙሪያ አጠር ያለ ዳሰሳ ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

(በዚህም ጽሑፍ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቃላትን ቃል በቃል ልተረጉማቸው ባለመቻሌ ወይም ብተረጉማቸውም ጽንሰ ሃሳቡን በጥሩ ሁኔታ ይገልጹታል ብዬ ስላላሰብኩ አልፎ አልፎ የእንግሊዝኛውን ቃል እንዳለ ተጠቅሜአለሁ፡፡ ለዚህም ከፍ ያለ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡)

## የጽንሰ ሃሳቡ ምንነት

“ልማታዊ መንግስት” የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን፣ የፖለቲካ ልሂቃንና ተመራማሪዎች የየራሳቸውን ትርጉም መስጠታቸውን ከተለያዩ ሰነዶች የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያዊ ምሁራን ከሰጡት ትርጉምና ትንታኔ እንጀምር፡፡

ስህን በቀለ እና ፀጋዬ ረጋሳ የተባሉ ኢትዮጵያውያን ከ“UNDP Ethiopia” ጋር ሆነው ባደረጉት ጥናት “ልማታዊ መንግስት” ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ ትርጉሞችን አቅርበዋል፡፡ ስህን እና ፀጋዬ እንዳቀረቡት ከሆነ፣ ልማታዊ መንግስት ማለት “በመንግስት የልማት እቅድ የሚመራ ኢኮኖሚ ያለው ሀገር” መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝም፤ “ልማታዊ መንግስት ማለት ከርዕዮተ ዓለም አኳያ የልማት አጀንዳ ያለው፣ የልማት አጀንዳዎቹንም ሊያስፈጽም የሚችል ቢሮክራሲ፣ መንግስታዊ ተቋማትና አደረጃጀት ያለው መንግስት ማለት ነው” ይላሉ እነ ስህን፡፡ ሌሎች ወገኖች ደግሞ “ልማታዊ መንግስት የልማት ግቦችን ለማስፈጸም የሚያስችል በቂ አደረጃጀት፣ ስልጣንና አቅም ያለው መንግስት ማለት ነው” በማለት እነ ስህን ካቀረቡት ትርጉም ጋር ተቀራራቢ (ተመሳሳይ) የሆነ ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡

አቢስ ጌታቸው የተባሉ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ሰው በበኩላቸው ልማታዊ መንግስት ከሁለት አቅጣጫዎች ሊታይ እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ ይህም “ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ” አቅጣጫዎች እንደሆነ ከገለጹ በኋላ፤ “ከኢኮኖሚ አኳያ ልማታዊ መንግስት ኢንዱስትሪውን እንዴት እንደሚገነባውና ገበያውን እንዴት እንደሚመራው ያለው እይታ የሚገለጽበት ሲሆን፤ ከፖለቲካ አኳያ ልማታዊ መንግስት የልማት ፖሊሲዎቹን የሚያስፈጽምበትን ፖሊሲ የሚያመለክት ነው” ይላሉ፡፡

የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን በበኩሉ ስለልማታዊ መንግስት ምንነት የራሱን ትርጉም ሰጥቷል፡፡ "የልማታዊ መንግስት ሞዴል በሶሻሊስታዊው በማዕከላዊ ፕላን የሚመራ የእዝ ኢኮኖሚ እና በኒዮሊበራሎቹ የነፃ ገበያ ስርዓት መካከል ያለ፣ በእውቀት ላይ የተመሰረተ፣ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገር የልማት አቅጣጫ ነው" ይላል የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን፡፡

በዚሁ ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ምርምር የሚያደርጉ ምሁራን በተደጋጋሚ ከሚያቀርቧቸው ትርጉሞች ውስጥ "ልማታዊ መንግስት ማለት፤ ከውጪ ድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎችን (Multi-National Corporations)፣ ከውስጥ የተቃዋሚ ፓርቲዎችንና የሰራተኛ ማህበራትን ተጽእኖ መቋቋም የሚያስችል ባህሪና ቁመና ያለውና ካቀደው የልማት ግብ ለመድረስ ተግቶ የሚሰራ መንግስት ማለት ነው" የሚለው ይገኝበታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ "ልማታዊ መንግስት ማለት ሕዝብንና ሀገራዊ ሀብትን አቀናጅቶና አስተባብሮ በመስራትና የልማት እቅዱን ተግባራዊ በማድረግ ግቡን ለማሳካት ሌት ተቀን የሚሰራ መንግስት ማለት ነው" የሚል ትርጉም የሚያቀርቡ ወገኖችም አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ "ልማታዊ መንግስት ማለት የውስጥም የውጪም ተጽእኖ የማያንበረክከውና እጁን የማይጠመዝዘው፣ [እንደ ጌኛ] ማንም ጭኖ የማይጋልበው፣ የሀገርና የህዝብ ሀብት ለመበዝበዝ ስልጣኑን የማይጠቀም፣... መንግስት ማለት ነው" የሚል ትርጉም ሰጥተውት እናገኛለን፡፡

በአንዳንድ የጥናት ሰነዶች ላይ ልማታዊ መንግስት ማለት ቀዳሚ ግቡን የኢኮኖሚ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ላይ ያደረገ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ በቅርብ የወጣ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ሪፖርት ላይ "ልማታዊ መንግስት ማለት ስልጣኑን፣ ታማኝነቱንና ሕጋዊነቱን ተጠቅሞ ልማታዊ ፖሊሲና ፕሮግራሞችን ቀርፆ በስራ ላይ በማዋል እድገትና ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት የሚሰራ መንግስት ነው" የሚል የልማታዊ መንግስት ትርጉም ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ጆን ናይት የተባሉ ምሁር በበኩላቸው "ልማታዊ መንግስት ማለት መንግስት ለፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የቅድሚያ ቅድሚያ (priority) የሚሰጥበትና ያ የልማት ህልም እንዲሳካ የሚከተለው የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው" ይላሉ፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ደግሞ ልማታዊ መንግስታት በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ እንደሚገቡና የያዙት የኢኮኖሚ እድገት እንዲቀላጠፍ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ፡፡ የጥናት ሰነዶቹ ላይ እንደተመለከተው፣ ልማታዊ መንግስታት ለእቅድ ትኩረት የሚሰጥ (Plan Rational) አቅጣጫን ይከተላሉ፡፡

"ልማታዊ መንግስት የሚለው የኢኮኖሚ ሞዴል ድህነትንና ስራ አጥነትን ለማስወድ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ መሣሪያ ነው" ይላል ጆንሰን፡፡ ልማታዊ መንግስታት ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት እቅድ አውጥተው እንደሚሰሩና ይህንንም እቅዳቸውን የሚያስፈጽም የሰለጠነና ክህሎት ያለው ሲቪል ሰርቪስ እንደሚያደራጁ ጆንሰን ጨምሮ ያስረዳል፡፡ ይህንንም የሰው ኃይል "የሰው ሀብት ልማት እቅድ" ይዘው በዩኒቨርሲቲዎች እንደሚያሰለጥኑና ዋነኛ ትኩረታቸውም ቴክኒካዊ ትምህርት ላይ እንደሆነ የጃፓንን ተሞክሮ በምሣሌነት በመጥቀስ ጆንሰን ያብራራል፡፡

ፒተር ኢቫንስ የተባሉ በመስኩ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁር በበኩላቸው "ልማታዊ መንግስት ማለት ጠንካራ መንግስት (Hard State) ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ልማታዊ መንግስት የልማት ፖሊሲ በማውጣት ሳይወሰን በማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ላይ ሕግ በማውጣት፣ ሥራ ላይ በማዋል፣ በመከታተልና በመቆጣጠር ጭምር ያሻውን እርምጃ

ስለሚወስድ ነው" የሚል ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ "ልማታዊ መንግስት እንደ አሜሪካ ካሉ ሬጉላቶሪ መንግስታት (Regulatory State) አሊያም ከስካንዲኔቪያን ሀገሮች ዌልፌር መንግስታት (Welfare State) የተለየ ነው፡፡ ልማታዊ መንግስት፣ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን አውጥቶ ሥራ ላይ የሚያውል፣ በፈለገው ጉዳይ ላይ አስፈላጊ ነው ባለው ጊዜ ጣልቃ እየገባ ሀገር የሚያስተዳድር፣ መንግስት ባለሀብትና ኢንቨስተር የሆነበት፣ የካፒታሊዝም ስርዓት (State Capitalism) ማለት ነው" ይላሉ፡፡

አንዳንድ ምሁራን ደግሞ "ልማታዊ መንግስት" የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በሁለት የሚከፈል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም "የ20ኛው ክፍለ ዘመን ክላሲካል አምባገነን ልማታዊ መንግስት" እና "የ21ኛው ክፍለ ዘመን ኮንቴምፖራሪ (contemporary) ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት" ብለው ይከፍሉታል፡፡ "ክላሲካል አምባገነን ልማታዊ መንግስት" የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጃፓንና የምስራቅ ኢስያ ሀገሮች ካስመዘገቡት የኢኮኖሚ እድገት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ "ኮንቴምፖራሪ ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት" የሚባለው ደግሞ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ቦትስዋናና ሞሪሼስ ያሉ ሀገሮች ያስመዘገቡትን እድገት የሚያመለክት መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

በክላሲካል ልማታዊ መንግስት ማህበራዊ ፖሊሲ ብዙም ትኩረት አይሰጠውም፡፡ ትኩረቱ ኢንዱስትሪን በማስፋፋት ላይ ነበር፡፡ የዚህ ዘመን (ኮንቴምፖራሪ) ልማታዊ መንግስት ትኩረት ግን "ከልማቱ የተገኘው ሀብት በማህበራዊ ፖሊሲ አማካይነት ህብረተሰብን ተጠቃሚ በሚያደርግ ተግባር ላይ መዋል አለበት፣ የህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል አለበት፣... ይህንን ያላደረገ መንግስት ልማታዊ መንግስት ሊሰኝ አይገባውም" የሚል ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ዘመን (ኮንቴምፖራሪ) ልማታዊ መንግስት ትርጓሜ ጋር አብሮ የሚገለጸው ጉዳይ ልማት የሀገርና በዚያ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች አጀንዳ በመሆኑ ሁለቱን አካላት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ልማት "ልማት" አደለም መባሉ ነው፡፡ እናም አንድ ልማታዊ መንግስት በሚያከናውነው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚፈጸም ሀገራዊ ፕሮጀክት መላው ሕዝብ እንደ አቅሙ የሚሳተፍበት መሆን እንዳለበት ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡ ሕዝብ ያልመከረበትና ያልተሳተፈበት የልማት ስትራቴጂ ልማታዊ ውጤት እንደሌለውም እነዚሁ ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡

ላውራ ሮትሌይ የተባሉ ተመራማሪ እንደሚሉት በአጠቃላይ ልማታዊ መንግስት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ይገለጽ የነበረው ጃፓንና 'የኢስያ ነብሮች' የሚባሉት ሀገራት ወደ ኢንዱስትሪ እድገት ካደረጉት ጉዞና ስትራቴጂ ጋር ተያይዞ ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ አስተሳሰብ ተቀይሮ ከሰው ሀብት ልማት (ኢቫንስ 2009) እና ሶሻል ዴሞክራቲክ ልማታዊ መንግስት ከመመስረት ጋር ተያይዞ እየተነገረ ነው፡፡ ይህም ብቻ አደለም፣ ልማታዊ መንግስት ከእነ ጃፓንና ኮሪያ ጋር ብቻ ሳይሆን ከኮስታሪካ፣ ሞሪሼስ፣ ቺሊ እና ህንድን ከመሳሰሉ ሀገሮች ጋር ተያይዞ እየተገለጸ መሆኑም ይታያል፡፡ ይህም ብቻ አደለም፣ የልማታዊ መንግስት ሞዴል እይታ ይበልጥ እየሰፋ መጥቶ "ልማታዊ መንግስት ማለት ዴሞክራሲያዊ መንግስት ማለት ነው" (ኢቫንስ 2009፣ ሳንድ ብሩክ 2007) እስከማለትና በዚህ ሞዴል ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ሀገሮችም አየርላንድ፣ ቦትስዋናና የስካዲኔቪያን ሀገሮችን እንደሚጨምር እየተነገረ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በአጠቃላይ፣ የልማታዊ መንግስትን ምንነት በተመለከተ ከላይ በዝርዝር ያቀረብናቸው ትርጓሜዎች፣ ትንታኔዎችና እይታዎች በጽንሰ ሃሳቡ ዙሪያ አንድና ወጥነት ያለው ግንዛቤ ሊያዝ አለመቻሉን ያመለክታሉ፡፡ በዚህ ረገድ፣ ፒተር ኢቫንስ እና ራውች የተባሉ

ምሁራን በ35 ሀገሮች ላይ ባደረጉት ጥናት "ልማታዊ መንግስት" በሚለው ማእቀፍ ወስጥ ያሉትን መንግስታት የሚያመሳስላቸው ልማት አፍቃሪነታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በስራ ላይ የሚያውሉት መንግስታዊ መዋቅርና የሲቪል ሰርቪስ አደረጃጀት የተለያየ መሆኑና ይህንንም ተከትሎ በእነዚህ ሀገሮች የተመዘገበው እድገትና ልማት የተራራቀ መሆኑ ጭምር ነው" ይላሉ፡፡

## ታሪካዊ አመጣጡ

"ልማታዊ መንግስት" የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መድረክ አምጥቶ ትንታኔ ያደረገው ቻልመርስ ጆንሰን የተባለ ምሁር ነው፡፡ ይህ ምሁር እ.ኤ.አ በ1982 ባቀረበው ጽሁፍ ጃፓን እ.ኤ.አ ከ1925 እስከ 1975 ባለው ጊዜ ያስመዘገበቺውን የኢንዱስትሪ መስፋፋትና የኢኮኖሚ እድገት በማንሳት ነው ትንታኔ ያደረገው፡፡ ከዚያ በኋላ ልማታዊ መንግስት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ሌሎች ተመራማሪዎችም አንስተው የምስራቅ ኢስያ ሀገሮችን የኢኮኖሚ ግስጋሴ ለመዳሰስ ተጠቅመውበታል፡፡ በዚህም መሰረት አመስደን የተባለ ምሁር እ.ኤ.አ በ1989 ስለ ኮሪያ፣ ዋዴ በ2004 ስለ ታይዋን፣... አንስተው የምርምር ውጤታቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣ ሌሎችም ምሁራን ስለ ሲንጋፖር፣ ስለ ማሌዥያ፣ ታይላንድና ሆንግ ኮንግ...ወዘተ. ተከታታይ ጥናት አድርገዋል፡፡

የእያንዳንዱ ሀገር መንግስት በሀገራዊ የኢኮኖሚ ልማት ላይ ሊኖረው ስለሚገባው ሚና ባለፉት ሃምሣ ዓመታት ክርክር ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ1945/46 ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካበቃ በኋላ እና የአፍሪካና የኢስያ አገሮች ከቅኝ ግዛት ከወጡ በኋላ የልማት አቅጣጫቸው በመንግስት ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት የሚራመድ ሲሆን፤ በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ ከቀድሞ ቅኝ ገዥዎች የተወረሱ መዋቅሮች የቀጠሉበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የተሰኘው ተቋም እ.ኤ.አ በ1958 የተቋቋመውም ይህንኑ የአፍሪካ ሀገሮች የልማት አቅጣጫ ለመደገፍ ነበር፡፡

እነዚህ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጡ ሀገሮች የኢኮኖሚ ሁኔታና የመንግስት መዋቅር ሲፈተሽ (በተለይም እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ) ለብክነት የተጋለጠ መሆኑ በተጨባጭ ታይቷል፡፡ በተለይም በላቲን አሜሪካ ሀገሮች፣ አዳዲሶቹ "እወደድ ባይ" (Populist) መሪዎች የተከተሉት ከለላን መሰረት ያደረገ ፖሊሲ የየሀገሮቻቸውን ኢኮኖሚ ካለበት ሊያነቃንቀው አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት እ.ኤ.አ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተለያዩ ምሁራን፣ የፖለቲካ ልሂቃንና ፖሊሲ አውጪዎች ጭምር በመንግስት ጣልቃ ገብነትና ነጋዴነት የሚመራ የኢኮኖሚ ልማት መቅረት እንዳለበትና በነፃ ገበያ በሚመራ የኢኮኖሚ ስርዓት መተካት እንዳለበት አስተያየት ይሰጡ ጀመር፡፡

በኢኮኖሚው ላይ የመንግስት ቁጥጥር ይቅር፣ በገበያ የሚመራ ነፃ የንግድ እንቅስቃሴ ይፈጠር፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የላቀ ሚና ይኑረው፣... የሚሉት ሃሳቦች ጎላ ብለው ይስተጋቡም ነበር፡፡ ባለፈው ጽሑፌ ላይ እንዳመለከትኩት በዓለም ባንክ እና በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት አማካይነት የተሰናዳው የዋሽንግተኑ ስምምነት አስር ያህል ቅድመ ሁኔታዎችን ደርድሮ ታዳጊ ሀገሮች የመዋቅር ማስተካከያ እንዲያደርጉ ግፊት ያደርግ የነበረውም በዚሁ ወቅት ነበር፡፡

የመዋቅር ማስተካከያና መሰል እርምጃዎች በአንዳንድ ሀገሮች ሀገራዊ የኢኮኖሚ መረጋጋትን መፍጠራቸው ቢታይም፤ የመንግስት ሚና እንዲቀንስ በመደረጉ በተለይም

በመሰረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ረገድ ክፍተት ፈጥሯል፡፡ በፕራይቬታይዜሽ ወደ ግል ይዞታ የዞሩት አንዳንድ ተቋማትም ውጤታማ ካለመሆናቸውም በላይ የሞኖፖሊ ሁኔታ በመፈጠሩ ብዙሃኑ ድሃ ህብረተሰብ ድጎማና የመንግስትን ድጋፍ ፈላጊ መሆኑ ታይቷል፡፡

በዚህም ምክንያት እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ አጋማሽ ላይ መንግስት በኢኮኖሚው ልማት ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ሚና በተመለከተ ለየት ያለ አስተያየት መንጸባረቅ ጀመረ፡፡ በወቅቱ ይቀርብ የነበረው አስተያየትም የምስራቅ ኢስያ ሀገሮች ያስመዘገቡትን የኢኮኖሚ ልማት መሰረት ያደረገ ነበር፡፡ እነዚህ የኢስያ ነብሮች (Asian Tigers) የተሰኙት (ሲንጋፖር፣ ሆንግ ኮንግ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን፣...) ሀገሮች ለሰላሳ ዓመታት ያህል ባደረጉት ጥረት ፈጣን የኢኮኖሚ እና የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሽግግር ማድረጋቸውና ከኋላ ቀር የግብርና ልማት ወደ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ እድገት መሸጋገራቸው ታይቷል፡፡ ይኸው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በቀጣይ ዓመታት በህንድ፣ በቻይናና በቬትናም በመሳሰሉት የኢስያ ሀገሮችም ተስፋፍቷል፡፡

ይህም በምስራቅ ኢስያ ሀገሮች የታየው የኢኮኖሚ ግስጋሴ መንግስታት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አዲስ አስተሳሰብ ይዞ ብቅ አለ፡፡ እነዚህ ሀገሮች የሄዱበት መንገድ የመንግስትን ሚና ብቻ ሳይሆን የመንግስት ተቋማትን ሚና በኢኮኖሚክስ ሳይንስ ማየት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ፡፡ በዚህም መሰረት በተደረገ ጥናት ሀገሮች ለማደጋቸው ወይም ላለማደጋቸው የተቋማት ሚና የንግድ እንቅስቃሴውን ነፃ ከማድረግ ወይም ካለማድረግ ከፍ ያለ መሆኑ ግንዛቤ ተወሰደበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የንብረት ባለቤትነትን የሚያረጋግጡ፣ ግጭትን የሚፈቱ፣ ሕግና ፀጥታ የሚያስከብሩ ተቋማት ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ መሆናቸው ታወቀ፡፡ የቻይና፣ የቦትስዋናና የሞሪሼስ ተሞክሮዎች ያሳዩትም ይህንኑ እውነታ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ የተቋማቱ ሚና ብቻም ሳይሆን የመንግስትም ሚና ጣልቃ ገባ አልገባ በሚል መንፈስ ሳይሆን የኢኮኖሚ ልማት ከማምጣት አኳያ እንደገና ሊፈተሽ እንደሚገባ ግንዛቤ ለማግኘት ተቻለ፡፡ የእነዚህ ሀገሮች እድገት ከተቋማቱ ጋር ብቻ ሳይሆን (በተለይ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ) ከመልካም አስተዳደር መኖር ወይም አለመኖር ጋር ጭምር መታየት እንዳለበት የሚያመላክቱ ተጨማሪ አከራካሪ አጀንዳዎች መነሳት ጀመሩ፡፡

እንዲህ ያለው የመልካም አስተዳደር ጉዳይ አጀንዳ ሆኖ የተነሳበት ምክንያት በሀገሮቹ መንግስት ከፍ ያለ ሚናና ኃላፊነት ከመያዙ አኳያ የሚሰጠው አገልግሎት በአቅም ማነስና በኪራይ ሰብሳቢነት በመዘፈቁ ብልሹነት የሚታይበት በመሆኑ በተለይም እርዳታ ሰጪ ሀገሮችን በማሳሰቡ እንደነበርም ይታወቃል፡፡

የተነሳው የመልካም አስተዳደር ጉዳይ “የመንግስት ሚና ይቀነስ” የሚል ሳይሆን “የመንግስት አቅም ተገንብቶ አገልግሎት አሰጣጡ ይጠናከር” የሚል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኪራይ ሰብሳቢነት ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ጋር ተያይዞ ከመቅረቡም በላይ ሰብአዊ መብት፣ ሙስና፣ ዴሞክራሲያዊ ሕጋዊነት (Democratic Legtimacy) ጋር ተያይዞ መቅረብም ጀመረ፡፡ በዚህም ምክንያት የልማታዊ መንግስት እና የመልካም አስተዳደር ጉዳይ አንዱ በሌላው ላይ ተደራርበው ይቀርቡ ጀመር፡፡ ልማታዊ መንግስት ሲባል ፈጣን አገልግሎት አሰጣጥን በውስጡ የያዘ ሲሆን፣ የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ደግሞ መንግስት ስልጣን የመቆጣጠሩን ሁኔታ ያመለክታል፡፡

## የልማታዊ መንግስት ባህሪ...

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ “ልማታዊ መንግስት” በሚለው ማእቀፍ ውስጥ ያሉ ሀገራት የሚከተሉት የዴሞክራሲ ስርዓት ወይም አምባገነንነት፣ በኢኮኖሚው ጣልቃ የሚገቡበት ሁኔታና የጣልቃ ገብነቱ ደረጃ እንዲሁም የሚከተሉት የኢንዱስትሪ ፖሊሲና ያስመዘገቡት የልማት መጠን የሚለያያቸው ሲሆን፤ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ፖሊሲ፣ ዓላማና ግብ አዘጋጅተው በመስራት እድገት ማስመዝገባቸው ደግሞ ያመሳስላቸዋል፡፡

ይህ ልዩነትና ተመሳሳይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ልማታዊ መንግስት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የአንድን ሀገር የልማት ግስጋሴ የሚያሳይበት የራሱ ባህሪያት አሉት፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምሁራንና ተንታኞች ከጃፓንና ከምስራቅ ኢስያ ሀገራት የኢኮኖሚ እድገት ተሞክሮ በመነሳት የልማታዊ መንግስት መገለጫ የሆኑ ዋና ዋና ነጥቦችን ነቅሰው በማውጣት ሌሎች ሀገሮችም ተግባራዊ ያደርጓቸው ዘንድ አመላክተዋል፡፡ *(በዚህ ረገድ ው ካሚንግስ እ.ኤ.አ በ1999፣ ሉዊስ በ2006፣ ጉድ በ2002 ያቀረቧቸውን የጥናት ውጤቶች ይመለከቷል)*

በልማታዊ መንግስት ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ አስቸጋሪውና አወዛጋቢው ጉዳይ “ልማታዊ መንግስት ናቸው” ተብለው በሚጠቀሱት ሀገሮች ያለው የዴሞክራሲ ሁኔታ ነው፡፡ “ልማታዊ መንግስት” በሚባሉት በበርካታዎቹ ሀገሮች የሚታየው አምባገነናዊ የመንግስት አስተዳደር ነው፡፡ በእነዚህ ሀገሮች ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ቢመዘገብም ዴሞክራሲ የሚባል ነገር አይታወቅም፡፡ በአንዳንዶቹ ሀገሮች የአንድ ፓርቲ ስርዓት የተጫነበት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤ በሌሎቹ ደግሞ የይስሙላ ምርጫ እየተደረገ አንድ ፓርቲ ለረዥም ዓመታት ስልጣን ላይ የሚቆይበት የአውራ ፓርቲ ስርዓት የሰፈነባቸው ሀገሮች መሆናቸው ይስተዋላል፡፡

በዚህም ምክንያት፤ አንዳንድ ወገኖች “ሀገሮቹ የኢኮኖሚ እድገት ስላስመዘገቡ ብቻ ልማታዊ መንግስት ሊባሉ አይገባም፡፡ ልማታዊነት በኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን በሀገሮቹ ካለው የዴሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብት አጠባበቅና በሀገሮቹ ከተመዘገበው የወንጀል መቀነስ ወይም መጨመር፣... አንጻር ጭምር መታየት አለበት” የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡

እንዲህ ያለው መከራከሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዘርፉ ለረጅም ጊዜአት ተከታታይ ጥናት በማድረግ የሚታወቁት ቻልመርስ ጆንሰን የልማታዊ መንግስት መገለጫ ናቸው ያሏቸውን አራት ነጥቦች አቅርበዋል፡፡ እነሱም፡- “**አንደኛ፤** አንድ ልማታዊ መንግስት፤ ቁጥሩ ትንሽ የሆነ፣ ብዙ የማይከፈለው፣ በተማረ የሰው ኃይል የተሞላ የመንግስት ቢሮክራሲ ሊኖረው ይገባል፣ **ሁለተኛ፤** ይህ የመንግስት ቢሮክራሲ ከመንግስት ተጽእኖ ነፃ ሆኖ በራሱ ተነሳሽነት የሚሰራ፣ ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ያለው ሊሆን ይገባል፣ **ሦስተኛ፤** ልማታዊ መንግስታት በሀገራቸው ኢኮኖሚው ውስጥ ከገበያ ስርዓት ጋር የማይቃረን የመንግስት ጣልቃ ገብነት የሚፈቅድ አሰራር ሊኖራቸው ይገባል፣ እና **አራተኛ፤** ልማታዊ መንግስታት ዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነታቸውን የሚመራ ተቋም ሊኖራቸው ይገባል” የሚሉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ የጆንሰን እይታዎች በተጨማሪ ሌሎች በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራንም የልማታዊ መንግስት ባህሪያትን ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ፤ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ሀገሮች ራሳቸውን በካፒታሊስት ወይም በኮሚኒስት ጎራ አባል እንዲያደርጉና ግንኙነታቸውም ከቡድናቸው አባላት ጋር እንዲሆን ግድ ይል ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ግን እንዲህ ያለው ርእዮተ ዓለምን መሰረት ያደረገ ቡድናዊነት ፈርሷል፡፡ ከዴሞክራሲያዊነት፣

ከሰብአዊ መብት አያያዝና ከመሳሰሉት አኳያ ዓለም አቀፍ ተጽእኖዎች ቢኖሩም፣ የምስራቅ ኢስያ ሀገሮች በኢንዱስትሪ ልማት በመመንደጋቸው ምርቶቻቸው በአሜሪካ ገበያዎች ጭምር ተፈላጊነት አላቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው በዚህ ዘመን ያሉ ልማታዊ መንግስታት ከግሎባላይዜሽን እና ከወጪ ንግድ ግንኙነት (export trade relation) አኳያ የተቃኘ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ያለው ግንኙነትም የልማታዊ መንግስት ባህሪ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

ሞካንዳዊሬ የተባሉ አፍሪካዊ ምሁር የልማታዊ መንግስት ዋነኛ መገለጫ "ልማትን ዋነኛ ተልእኮዬ ነው ብሎ ተቀብሎ ያንን ተልእኮውን ለማሳካት ሌት ተቀን መስራቱ ነው" ይላሉ፡፡ አያይዘውም "እንዲህ ዓይነት አቋምና ርእዮተ ዓለም የሌለው መንግስት ልማትም አያመጣም፣ ድህነትንም አያስወግድም…" ይላሉ ምሁሩ፡፡ ሰብአዊ መብት ያልተከበረበት፣ ዴሞክራሲ ያልሰፈነበት ሀገር… የተሟላ ልማታዊ መንግስት ሊሰኝ አለመቻሉንም ሞካንዳዊሬ ያስረዳሉ፡፡

የልማታዊ መንግስት ሞዴልን በሚከተሉ ሀገራት ቢሮክራሲው የሀገርን ኢኮኖሚ በማሳደጉ ረገድ የላቀ ሚና እንዲጫወት ትኩረት ያደርጋል፡፡ በጆንሰን ጥናት የልማታዊ መንግስት ሞዴል ተደርጋ በቀረበቺው ጃፓን ሲቪል ሰርቪሱ ከፖለቲካ ኃይሎች ተጽእኖ ነፃና ገለልተኛ ነው፡፡ በተለይም የጃፓንን የወጪ ንግድ የሚመራው የጃፓን ዓለም አቀፍ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ እና በ1970ዎቹ የጃፓንን ኢንዱስትሪዎች በመምራትና ኢኮኖሚውን በማሳደግ ከፍ ያለ ሚና ነበረው፡፡

በጃፓን ቢሮክራሲ ውስጥ የሚሰሩ የመንግስት ሠራተኞች ከታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረቁና ከፍተኛ የስራ ተነሳሽነት ያላቸው ነበሩ፡፡ በጃፓን የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች ሲቀጠሩ የብቃት ማረጋገጫ ፈተናዎችን ያለፉ እንዲሆኑ ሲደረግ፣ በየወቅቱ የተለያዩ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችም በተከታታይ ይሰጣቸው ነበር፡፡ እነዚህ ስልጠናዎች አስተዳደራዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት ስለሚረዷቸው ፖለቲከኞች ጣልቃ አይገቡባቸውም፡፡ የመንግስት ሰራተኛውና የግሉ ሴክተር በእኛ ሀገር እንደሚታየው "በሌባና በፖሊስ" ዓይነት ሳይሆን በተቀናጀና በከፍተኛ የትብብር መንፈስ ይሰሩም ነበር፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩት የልማታዊ መንግስት ባህሪያት ምን መሆን እንዳለበት ነው፡፡

ሌላው የልማታዊ መንግስት መገለጫ ተደርጎ እየተወሰደው ያለው ነገር፤ የልማታዊ መንግስት ሞዴልን እየተከተሉ ባሉ ሀገሮች ያሉ ገዢ ፓርቲዎች ለራሳቸው "አውራ ፓርቲ" የሚል ስም ሰጥተው ለረዥም ዓመታት ስልጣን ላይ የመቆየታቸው ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በጃፓን ሃምሣ ዓመታት፣ በቦትስዋና አርባ ስምንት ዓመታት፣ በደቡብ አፍሪካና በኢትዮጵያ ከሃያ ዓመታት በላይ የቆዩ ፓርቲዎች ጥሩ ምሣሌዎች ናቸው፡፡

ልማታዊ መንግስት ሁለት ነገሮች ሊኖሩት እንደሚገባው አንዳንድ ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡ **አንደኛ፡-** የልማታዊነት ርዕዮተ ዓለም (developmental ideolody) ሲሆን፣ **ሁለተኛ፡-** የልማቱን ሂደት ለመምራትና ግቦቹን ለማሳካት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትና ስታንዳርድ ያላቸው ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች የልማታዊ መንግስት "ሶፍትዌር" እና "ሃርድዌር" ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

በሌሎች የምርምር ሰነዶች ላይ እንደተገጸው አንድ ልማታዊ መንግስት የሚከተሉት ባህሪያት ይኖሩታል፡፡ "**አንደኛ፤** ምርጫ በመጣ ቁጥር ተጠርጌ እወጣለሁ ብሎ የማይሰጋ፣ ከፖለቲካ ተጽእኖ ገለልተኛ የሆነ፣ በፖለቲካ ታማኝነቱ ሳይሆን በእውቀትና በችሎታው

የተቀጠረ የመንግስት ሰራተኛ፣ **ሁለተኛ፤** ጠንካራ፣ ራዕይ ያለው፣ የመምራት አቅም ያለው፣ ቁርኛ አመራር፣ **ሦስተኛ፤** በተግባር ሊተረጎም የሚችል የልማት እቅድ፣ **አራተኛ፤** የተቀናጀ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና አስተማማኝ ሀብት፣ **አምስተኛ፤** ወደ አገራዊ ከበርቴነት የሚሸጋገር የልማት ኃይል የሆነ ሀገራዊ ባለሀብት ድጋፍ፣ **ስድስተኛ፤** ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረተ ልማት፣ ሀገራዊ የሰው ኃይሉን በእውቀት የሚያንጽ የትምህርት ስርዓት፣ ህብረተሰብ-ተኮር የጤና፣ የመኖሪያ ቤት፣... ወዘተ. ማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት፣ እና **ሰባተኛ፤** የመንግስትን ተዓማኒነትና የህግን የበላይነት የሚያረጋግጡ ተቋማትና የአሰራር ስርዓት፣ አስተማማኝ ሰላም፣ የተረጋጋ የፖለቲካ ምህዳር" የሚሉት ናቸው፡፡

"ኢኮኖሚን መሰረት ያደረገ ሀገር ወዳድነት (Economic Nationalism)፣ የውጭ ቴክኖሎጂን የመቅዳት ዝንባሌ፣ ሰፊ የመንግስት መዋቅር፣ ለቴክኒካዊ ትምህርት ትኩረት መስጠት፣ የፖለቲካ ምህዳር መሻሻል፣ ለኢኮኖሚ እድገት ቅድሚያ መስጠት፣..." የልማታዊ መንግስት ባህሪያት ናቸው የሚሉ ወገኖችም አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ልማታዊ መንግስታት በሚከተሉት የልማት ፖሊሲ አማካይነት "የኢኮኖሚ እድገት ምጣኔ ያሳድጋሉ፣ ድህነት ይቀንሳሉ፣ ስራ አጥነትን ያስወግዳሉ፣ ለህብረተሰብ እኩል ተጠቃሚነት ይሰራሉ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ያስፋፋሉ፣.." በማለት ይገልጿቸዋል፡፡

ስህን በቀለ እና ፀጋዬ ረጋሳ ባቀረቡት ጥናት የልማታዊ መንግስታት ዋነኛ ባህሪ "ከጥገኛነት ለመውጣት፣ ከድህነት ለመላቀቅና ራስን ለመቻል አቅደው መስራታቸው ነው" ይላሉ፡፡ ግባቸውም "ከኒዮሊበራሊዝም ተጽእኖ ነፃ ሆኖ በኢኮኖሚ በማደግ መበልጸግና መልማት" መሆኑን እነ ስህን ያብራራሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ የልማታዊ መንግስት መሰረታዊ ዓላማ "ዜጎችን ከገበያ ኃይሎች ወረራ በመከላከል ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳድጉና ሀገራቸውን እንዲያበለጽጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት" መሆኑ በበርካታ የጥናት ሰነዶች ላይ ተገልጿል፡፡ እነዚህም ተግባራት የልማታዊ መንግስት መገለጫዎች ተደርገው የሚወሰዱ ባህሪያት ናቸው፡፡

## ክርክሩ…

የልማታዊ መንግስት ሞዴል የሚከተሉ ሀገሮች በኒዮሊበራሊስቶች ከሚሰነዘርባቸው ትችት አንዱ "ልማታዊ መንግስታት አላስፈላጊ ወጪ (ብክነት) ያበዛሉ፡፡ ገበያው ራሱን በራሱ እንዲመራ ቢያደርጉት አላስፈላጊ ወጪዎች ይቀንሳሉ፡፡ ገበያውን ነፃ ባለማድረጋቸው የንግዱ ማህበረሰብ አባላት መንግስት ከለላ እንዲያደርግላቸውና አንዳንድ ፖሊሲዎችን እንዲያሻሽልላቸው የእጅ መንሻ (ጉቦ) በመስጠት ለአላስፈላጊ ወጪ (ለኪራይ ሰብሳቢነት) ይዳረጋሉ" የሚል ነው፡፡

የልማታዊ መንግስትን ንድፈ ሃሳብ የሚያቀነቅኑ ወገኖች በበኩላቸው "ገበያው ራሱ ይወስን ብሎ ሁሉን ነገር ለገበያ መልቀቅ የገበያ ውድቀትን (Market Failure) ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም የገበያው ተዋናይ የሆኑት ግለሰቦች በተበታተነ ሁኔታ በተናጠል የሚያደርጉት ውሳኔ የእቃዎችን ዋጋ ወይ አለቅጥ ያንራል ወይ አለቅጥ ዝቅ ያደርጋል፡፡ ይህም የገበያውን ዋጋ ትክክለኛነት (Rationality) እንዲዛባ ያደርጋል፡፡ እናም በእንደዚህ ያለ ጊዜ መንግስት ጣልቃ ገብቶ የሚሰጠው ውሳኔ ገበያውን ያረጋጋል፡፡ መንግስት እንዲህ ያለ የማረጋጊያ እርምጃ ካልወሰደ ግን የገበያ ውድቀት ብቻ ሳይሆን የመንግስት ውድቀት አይቀሬ ይሆናል..." ይላሉ፡፡

“ሌላው...” ይላሉ እነዚሁ የልማታዊ መንግስት ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች “... ሌላው ኒዮሊበራሊስቶች ‘ነፃ ገበያ’ ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ ያለ ትርጉም አላስቀመጡም፡፡ የገበያው ነፃነት እስከምን ድረስ ነው? የሚለውም አይታወቅም፡፡ ይህ ሁኔታ ትርጉም ካልተቀመጠለትና ወሰን ካልተበጀለት ሁሉም ነገር ግምታዊ ይሆናል፡፡ ግምት ደግሞ ከሰው ሰው ይለያያል...” በማለት መከራከሪያቸውን ያቀርባሉ፡፡

በልማታዊ መንግስት አቀንቃኞችና በኒዮሊበራሊስቶች መካከል የሚነሳው ሌላው የመከራከሪያ ሃሳብ፤ ኒዮሊበራሊስቶች ታዳጊ ሀገሮች የሚከተሉትን የልማታዊ መንግስት ሞዴል በአንድ በኩል “የሕዝብን ስሜት ለመሳብ የታለመ እወደድ ባይነት (Populist) ነው” ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ “የመንግስት መዋቅር (ቢሮክራሲው) ደካማ ነው፣ የሚከተሉት ፖሊሲ የተሳሳተ ነው፣ ያስቀመጡት ግብ ሊፈጸም የማይችል ነው፣...” በማለት ያጣጥላሉ፡፡

እነዚህ ትችቶች ላይ ላዩን ሲታዩ የታዳጊ ሀገሮችን ቴክኒካዊ ብቃት የሚነቅፍ ቢመስልም ዋነኛ ዒላማው ፖለቲካዊ አንደምታ እንዳለው እንደ ሀ ጁን ቻንግ ያሉ የልማታዊ መንግስትን ንድፈ ሃሳብ የሚደግፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ እንደ እነዚህ ምሁራን ከሆነ፤ የኒዮሊበራል ደጋፊ ኢኮኖሚስቶች ራሳቸው በታዳጊ ሀገሮች ላይ በግልጽ የሚታይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ዘመቻ ከፍተው ጥቃት እየሰነዘሩ ዘወር ብለው ደግሞ “ታዳጊ ሀገሮች የፖለቲካ ጉልበታቸውን እየተጠቀሙ ነው፡፡ እንዲህ ያለው አካሄድ ደግሞ ትክክለኛ የኢኮኖሚ ስርዓት መፍጠር አያስችላቸውም፡፡ አስተውሎት የጎደለው፣ ምክንያታዊ ያልሆ (irrational) የፖለቲካ ጣልቃገብነት ስለሆነ ፖለቲካው ከኢኮኖሚው መለየት አለበት...” የሚል እርስ በርሱ የሚቃረን ትችት ይሰነዝራሉ፡፡

“የተለያዩ ግለሰቦችና የኅብተሰብ ክፍሎች ያሏቸው ልዩነቶች በገበያ ውድድር ይፈታል እንጂ በፖለቲካ ውሳኔ እንዲቻቻል አይደረግም፡፡ ይህ ልዩነት በፖለቲካ ጣልቃ-ገብነት እንዲቻቻል ይደረጋል ከተባለ ግን የፖለቲካ ስልጣን ከያዘው ኃይል ጋር የወገኑትን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው የሚሆነው...” የሚል ተጨማሪ መከራከሪያ ያቀርባሉ የኒዮሊበራል ርዕዮት ደጋፊ ኢኮኖሚስቶች፡፡ የልማታዊ መንግስት ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች በበኩላቸው “የፖለቲካ እጆችን የመሰብሰቡ አካሄድ በፒኖቼ ዘመን በቺሊ ተሞክሮ የተሟላ ውጤት ሊያመጣ እንደማይችል በተግባር ታይቷል” ይላሉ፡፡ አክለውም “በየትኛውም አካሄድ ቢኬድ ከልማቱ ተጠቃሚ ሊሆን የማይችል የህብረተሰብ ክፍል መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ መንግስት ብዙሃኑን የኅብረተሰብ ክፍል የሚወክል እስከሆነ ድረስ የፖለቲካ አመራሩ በአርቆ አሳቢነት መንፈስ የሚወስደው እርምጃ ብዙሃኑን የሚጠቅም ይሆናል” በማለት ይከራከራሉ፡፡

በአጠቃላይ በልማታዊ መንግስት ንድፈ ሃሳብ ዙሪያ የሚነሱት አሉታዊና አዎንታዊ ክርክሮች ከላይ በአጭሩ የተጠቀሱትን የሚመስሉ ሲሆን፤ በኒዮሊበራሊዝም እና በልማታዊ መንግስት ሞዴል ዙሪያ እየተደረገ ያለው የርእዮተ ዓለም ግብግብ ከቀዝቃዛው ጦርነት ወዲህ ዓለምን እንደገና ወደ ሁለት ጎራ የመክፈል ውጤት ሊኖረው እንደሚችል አስባለሁ፡፡

*መደምደሚያ*

ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው፣ “ልማታዊ መንግስት” የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በተመለከተ አንድ ወጥ የሆነ ትርጓሜም ሆነ መስፈርት የሌለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የልማታዊ መንግስት አቅጣጫን የሚከተሉ መንግስታት አገልግሎት አሰጣጣቸውን

ቀልጣፋ ለማድረግና የሀገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የፖለቲካ ቁርጠኛነት ያላቸው መሆኑም ታይቷል፡፡ ዋነኛው መገለጫቸውም ይኸው ነው ይላሉ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን፡፡

ሌላው መታወቅ የሚገባው ጉዳይ፣ ልማታዊ መንግስት ማለት ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍ ያለ ሚና እንዲኖረው የሚያደርግ ንድፈ ሃሳብ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል ነው ልማታዊ መንግስታት የኢኮኖሚ እድገትን ቀዳሚ የመንግስት አጀንዳ አድርገው ፖሊሲ የሚያወጡትና በተከታታይም የልማት ግባቸውን ለማሳካት የሚያስችሉ ተቋማትን በማደራጀት፣ ሀገራዊ ኢኮኖሚው የተረጋጋ እንዲሆን የተለያዩ ሕጎችን በማውጣት፣ ጠንካራ የፍትህ ስርዓት በመዘርጋት፣ የግጭት መፍቻ ስርዓት እንዲኖር በማድረግ፣... ሥራ ላይ ተጠምደው የሚታዩት፡፡

የልማታዊ መንግስት ሞዴልን የሚከተሉ ሀገሮች ሀገራዊ ልማትና እድገት ላይ ያተኮሩበት የተለያየ ምክንያት አላቸው፡፡ ጃፓን ልማት ላይ ያተኮረችበት ምክንያት በሀገሪቱ ላይ ተደጋጋሚ የኢኮኖሚ ቀውስ በመከሰቱ ከእንደዚያ ዓይነት ህዝብን የሚፈጅ ችግር ለመላቀቅ ሲሆን፤ ደቡብ ኮሪያ ከሰሜን ኮሪያ እንዲሁም ታይዋን ከቻይና የሚሰነዘርባቸውን ዛቻና ማስፈራራት በቴክኖሎጂ በመታገዝ ኢኮኖሚያቸውን አጠናክረው ለመመከት መሆኑ ይነገራል፡፡ ቻይናን በተመለከተ ስልጣን ላይ ያለው ኮሙኒስት ፓርቲ ፖለቲካዊ ህጋዊነቱን (Political Legtimacy) ለማረጋገጥ ሲል የህዝቡን ሕይወት የሚለውጥ የልማት መስመር መከተልን መርጧል፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ለዘመናት በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የኖረውን ድህነት ለማስወገድ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ ሌሎች ሀገሮች የልማታዊ መንግስት ሞዴል የመረጡበትን ምክንያት በተመለከተ "የፖለቲካ ስልጣንን ለረጅም ጊዜ ጠብቆ ለመቆየት የኢኮኖሚ ጥንካሬ አስፈላጊ በመሆኑ ነው" የሚለው አስተያየት በተለያዩ ሰነዶች ላይ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡

በርካታ የልማታዊ መንግስት ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች፣ ለአንድ ሀገርና ሕዝብ ዴሞክራሲም ልማትም እንደሚያስፈልጉት ይቀበላሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ "አንድ የልማት ፖሊሲ በአንድ የምርጫ ዘመን ተፈጽሞ ሀገርን የሚለውጥ ልማት በአጭር ጊዜ ሊገኝ ስለማይችል ልማታዊ መንግስታት የጀመሩትን የልማት ፖሊሲ እስከሚፈጽሙ ድረስ ዴሞክራሲያዊ መሆን አይጠበቅባቸውም... እናም ለሰላሳ ወይም ለሃምሳ ዓመታት አንድ ፓርቲ በተደጋጋሚ በምርጫ የሚያሸንፍበት የአውራ ፓርቲ ስርዓት አስፈላጊ ነው..." የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡ ይህንን አስተሳሰብ የሚቃወሙ አስተያየት ሰጪዎች በበኩላቸው "ይሄማ ዴሞክራሲን በልማት የመቆመር ፖለቲካ ነው" ይላሉ፡፡

ላለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ያለው ገዢ ፓርቲ መሪዎች ይህንን ሁኔታ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ለዚህም ነው እከተለዋለሁ የሚሉት የልማታዊ መንግስት ሞዴል "ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት" እንደሆነ ደጋግመው የሚነግሩን፡፡ ይህም ማለት በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የልማታዊ መንግስት ሞዴል 'ልማትን ገለል አድርጎ ዴሞክራሲ ላይ የተቸከለ ወይም ዴሞክራሲን ረስቶ ልማት ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ልማትንም ዴሞክራሲንም አብሮ የሚያስኬድ ነው' ይላሉ ኢህአዴጎች፡፡

ኢህአዴጎች ይህንን ብለው ቢያቆሙ መልካም ነበር፡፡ ዘወር ብለው ደግሞ በሀገራችን እየተፈጠረ ያለው የአውራ ፓርቲ ስርዓት መሆኑን ይገልጹልናል፡፡ *(ይህንን በተመለከተ አዲስ ራዕይ መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር 3 እትም ከገጽ 27 - 34 ይመለከቷል)* የአውራ ፓርቲ ስርዓት ደግሞ ከቻይና የተሻለ መሆኑን ከመግለጽ በላይ ዴሞክራሲያዊነቱ ድምፅን ከፍ አድርጎ የሚወራለት አለመሆኑ ይታወቃል፡፡

- ይህ ጽሑፍ ዛሬ ታህሳስ 14 ቀን 2007 በወጣው ኀብረ-ብዕር መጽሔት ቅጽ 01 ቁጥር 03 እትም ላይ ቀርቧል፡፡ መጽሔቱን ያላገኙ እንዲያነቡትና ለመወያያም ይሆን ዘንድ በዚህ ዌብሳይት ላይ እንዲታተም ተልኳል፡፡